አሐዱ ባንክ
Ahadu Bank
ከብዙዎች ለብዙዎች
Inclusive Intermediation
ahadubank.com

ይቻላል
It's Possible!

ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ.
Tsehay Insurance S.C.
ፀሐይ ለሁሉም ታበራለች!!
The Sun Shines For All !!
ቦሌ ድልድይ ከብራስ ሆስፒታል ፊትለፊት
Bole Bridge, in front of Brass Hospital
Tel.+251 111 11 97 70/71 +251 111 11 98 27/97 93
Fax: +251 111 11 98 86
Website: www.tsehayinsurance.com
E-mail: marketingd@tsehayinsurance.com



አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# ንግድና ልማት

ጥቅምት 2016 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com


## የቼክ ሪፐብሊክ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ መዋለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ጥሪ ቀረበ

**በከፍያለው ዋሲሁን**



አዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከቼክ ኢንዱስትሪ ኮንፌደሬሽን በጋራ ለመስራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል:: በቼክ ጠቅላይ ሚንስትር ፒተር ፊይል የተመራ እና 14 የቼክ ኩባንያዎች ያቀፈው የንግድ ልዑክ በአዲስ አበባ ተገኝቶ ከኢትዮጵያዊያን ነጋዴዎች ጋር በጋራ መሰራት በሚችሉበት ዙሪያ ተወያይተዋል ::

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቁልፍ አጋሮች መካከል አንዷ መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚንስትር ፊያላ ፣ ሀገራቸው ቡናን ከመሸመት ባለፈ በንግድና እና ኢንቨስትመንት የትብብር እድሎችን እድል የምንሰጠበት ጌዜ ላይ እንገኛለንነ ብለዋል::

የኢፌድሪ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ደኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አረጋ በበኩላቸው ሁለቱ አገራት ያላቸው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ቢሆንም ፣ በኢኮኖሚው ዘርፍ ብዙም ሰኬታማ አለመሆኑን ገልፀዋል::
በኢትዮጵያ በደርግ ዘመን ዘመን የተቋቋሙት አዲስ ጎማ ፋብሪካ ፣ ሀረር እና በደሌ ቢራ ፍብሪካዎች ፣ ኮምቦልቻ እና አርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ፣ ሃዋሳ ዱቄት ፋብሪካ ፣ ሞጆ ቆዳ ፋብሪካ እና መልካ ዋካና የአሌክትሪክ ማመንጫ የተቋቋሙት ከያኔዋ ቼክዝላቢያ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ መገንበታቸውን አስታውሰዋል :: ሁለቱ አገራት በኢኮኖሚው ዘርፍ ረጅም አመት ያስቆጠረ ትብብር እንዳለ ጥሩ ማሳያ መሆኑን አምባሳደር ምስጋኑ ገልጸዋል::

አክለውም የውጭ አገር ባለሃብቶች አስቻይ ከባቢ በመፍጠር ንግድና ኢንቨስትመንትን የበለጠ ለማጠናከር መንግሰታቸውን ቁርጠኛ መሆኑን ገልፀዋል :: በመሆኑም የቼክ ሪፐብሊክ ባለሃብቶችና መንግስት በግብርና፣ ማምረቻው ዘርፍ ፣ፋርማሲቲካል ፣ ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጅ ፣ በማዕድን ፍለጋ እና የማዕድን ምርቶችን ማልማት ዘርፍ ላይ በኢትዮጵያ መዋለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ጥሪ አቅርበዋል :: የአዲስ ቻምበር ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሽንቁጤ በበኩላቸው ኢትዮጵያ ለቼክ ኩባንያዎች ገበያ መሆኗን ጠቅሰዋል :: በኢትዮጲያ በቆዳ ፣ መሰረተ ልማት ፣ሲሚንቶ እና ቴክኖሎጅ ዘርፎች ያሉ የኢንቨስትመንት እድሎችን

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## አዲስ ቻምበር የፋይናንስ ዘርፉን መረጃ የያዘ አልማናክ እያዘጋጀ መሆኑን ይፋ አደረገ

የፋይናንስ ዘርፉ ለኢኮኖሚው መሻሻል እንዲሁም ለንግድ እና ኢንቨስትመንት መስፋፋት ሚናው ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ንግድ ምክር ቤቱ በተለያዩ አገልግሎቶች ዘርፉን ሲደግፍ መቆየቱ ይታወሳል::
በሃገራችን ውስጥ የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት የተደራጀ መረጃዎችን እንዲሁም ወቅታዊ የሆኑ ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እንዲይዝ ተደርጎ በምክር ቤቱ የሚዘጋጀው አልማናክ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ ባለሃብቶች የሃገር ውስጥ የፋይናንስ እድገትን የሚያመላክቱ መረጃዎችን የሚያገኙበት፣የቴክኖሎጂ መሻሻሎችን፣አዳዲስ አሰራሮችን እንዲሁም ከዘርፉ ጋር የተገናኙ የጥናት ውጤቶችን በቀላሉ እንዲያገኙ ተደርጎ የሚዘጋጅ ነው ተብሏል::

የሚዘጋጀው አልማናክ የሞባይል መተግበርያ ያለው በመሆኑ ተደራሽነቱን ለመጨመር እንደሚረዳው ተጠቁሟል፡ ፡ ባንኮች ኢንሹራንሶች ፣አነስተኛ የብድር ተቋማት፣የፋይናንስ ቴክኖሎጂዎች እና በፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ ያሉትን ያካትታል፡ ፡ ምክር ቤቱ በሚያዘጋጀው አልማናክ ላይ የሚሳተፉ የፋይናንስ ተቋማት አዳዲስ አገልግሎቶቻቸውን የምክር ቤቱ ተደራሽነት ባለበት ሁሉ ለማስተዋወቅ የሚያግዛቸው ሲሆን ከሃገር ውስጥ አልፎ በሌሎች ሃገሮችም ደንበኞችን ለማፍራት አይነተኛ መንገድ እንደሚሆን ተጠቅሷል::

## አዲስ ቻምበር በአዲስ አበባ ከሚገኘው የፓኪስታን ኤምባሲ ጋር በኢትዮያና ፓኪስታን መካከል ያለው የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት በሚጠናከርበት ሁኔታ ላይ ተወያዩ





**በስታፍ ሪፖርተር**

ከቅርብ አመታት ወዲህ የፓኪስታን ሪፓብሊክ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት እንዲጠናከር ፍላጎት እያሳየች ትገኛለች:: የፓኪስታን የንግድ ልኡካን ወደ ኢትዮጵያ ከመላክ አንስቶ የንግድና ኢንቨስትመንት ስምምነቶችን በሀገራቱ መካከል እንዲፈረም መደረጉ ሁለቱ ሀገራት ኢኮኖሚያዊ ትስስራቸውን ለማጠናከር የሚያሳዩትን ቁርጠኝነት ያመላክታል::

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ**

**50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirmamecha@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
ከፍያለው ዋሲሁን
ካሳሁን ማሞ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ዘካሪያስ አሰፋ-ሰብሳቢ
ሲሳይ ታደሰ- አባል
ካሳሁን ማሞ- አባል
አሸናፊ ምትኩ- አባል
ስዩም ጫኔ -አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
ጥቅምት 2016 እትም

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# ርዕሰ አንቀጽ

## ለአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ዘላቂ እድገትን እውን እናድርግ!

ግብርና ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር ሲሆን፣ ከአገሪቱ አጠቃላይ ህዝብ 80 በመቶ የሚሆነውም ኑሮው በግብርና ላይ የተመሰረተ ነው። በኢትዮጵያ ጥቅል አገራዊ ምርት 39 በመቶ ድርሻ ያለው የግብርናው ዘርፍ፣ አገሪቱ ከወጪ ንግድ ገቢ ከምታገኘው የውጭ ምንዛሬም 90 በመቶ ድርሻ ይይዛል።

ኢትዮጵያ ለወጪ ንግድ የምታቀርበው የግብርና ምርት በአብዛኛው ያልተቀነባበረ ሲሆን ከነዚህም መካከል ቡና፣ የቅባት እህሎች፣ ቅመማ ቅመም፣ የቁም እንስሳትና አበባ ይገኙበታል። የአግሮ ኢንዱስትሪው ዘርፍ በአንጻሩ ለኢትዮጵያ ጥቅል አገራዊ ምርት ያለው ድርሻ 5 በመቶ ያህል ብቻ ሲሆን፣ ግማሽ ያህሉ የአገሪቱ የማኑፋክቸሪንግ ወይም አምራች ዘርፍ ምርት ግን የምግብና መጠጥ ምርት ነው። ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ የግብርና ስርዓቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የተለያየ አይነት ስነ ምህዳር፣ ሰፊና ሊታረስ የሚችል መሬት እና በቂ የሰው ሃይል ጉልበት ባለቤት ናት።

የግሉ ዘርፍ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ፕሮግራሞች ዋነኛ አካል መሆኑ ከጊዜ ወደጊዜ የተሻለ እውቅናና ትኩረት እየተሰጠው ይገኛል። የግብርና ምርቶች ማቀነባበርያ ዘርፍ መንግስትም ሆነ የግሉ ዘርፍ ተቀዳሚ ትኩረት ሊሰጧቸው ከሚገቡ ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ እንደሆነ በጽኑ ይታመናል። በመሆኑም በኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች ማቀነባበርያ ዘርፍ ውስጥ የሚታዩ እንቅፋቶችን ለይቶ በማውጣት ዘላቂ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴን ፤ የስራ እድል ፈጠራንና ክልላዊና አገርአቀፋዊ የንግድ ትስስርን እውን ማድረግ ያስፈልጋል።

የግብርና ማቀነባበር ዘርፍ ምንም እንኳን በመንግስት ፖሊሲ ተቀዳሚ ትኩረት የተሰጠውና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ፍላጎትም እያደገ የመጣበት የንግድ ዘርፍ ቢሆንም፣ የተለያዩ ማነቆዎች ዘርፉ በሚፈለገው መልኩ እንዳያድግ አድርገውታል። የጥሬ ዕቃዎች አቅርቦት፣ ማርኬቲንግ እንዲሁም የድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ዝቅተኛ መሆን፤ መሰረተ ልማትና ፋይናንስ ዋነኛ የዘርፉ እንቅፋቶች መሆናቸውን ቀጥለዋል።

አዲስ ቻምበር የግብርና ኢንዱትሪ ዘርፍ ያለውን እምቅ አቅም ለማሳደግ ዘርፉን በሚገባ ማስተዋወቅ ወሳኝ ድርሻ እንዳለው በጽኑ ያምናል። ከዚህ አንጻር ምክር ቤቱ ለበርካታ አመታት አለምአቀፍ የእርሻና የምግብ አውደ ርዮችን በማዘጋጀት በግብርና ማቀነባበር የገበያ እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚገኙ ተዋንያን የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ፤ የግብርና ቴክኖሎጂን እንዲቀስሙ እና የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ የበኩሉን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል። ስለሆነም መንግስትም ሆነ ሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ምክር ቤቱ የግብርና ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ የሚያደርገውን ጥረት በመደገፍ የተሻለ ሀገርና ኢኮኖሚ እንዲፈጠር ጥሪውን ያቀርባል።

# የቼክ ሪፐብሊክ ኩባንያዎች  በኢትዮጵያ መዋለ...

ከ ገጽ 1 የዞረ

የቼክ የቢዝነስ ድርጅቶች አልተጠቀሙም ብለዋል::
በሁለቱ አገራት መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ በአውሮፓዊያኑ 2022 11 ነጥብ 3 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር መሆኑን የጠቀሱት ወ/ሮ መሰንበት 11 ሚሊየን ዶላር ድርሻ ቼክ ወደ ኢትዮጵያ ልካ ያገኘችው ነው :: ይህም የሚያሳየው የንግድ ሚዛኑ ወደ ቼክ ያደላ መሆኑን ነው ብለዋል::
የንግድ ግንኙነቱ ሀገራቱ ካላቸው አቅም ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ የሚባል ነው ብለዋል ::

ኢትዮጵያ በዋናነት ቡና ለቼክ የምትልክ ሲሆን ፤ የማቀነባበሪያ መሳሪያዎች ፣ የአውሮፐላን ክፍሎች ፣ ብረት እና ሌሎች የኢንዱስትሪ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ ታስገባለች ብለዋል :: በመሆኑም የሁለቱ አገራት ያላቸውን ግንኙነት እና የተቀናጀ የኢኮኖሚ አቅማቸውን በመጠቀም አጋርነታችቸውን ከፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል ብለዋል ::

የቼክ ኢንዱስትሪ ኮንፌደሬሽን ፕሬዝዳንት ጃን ረፋጅስ ኮቪድ 19 በሁለቱ አገራት የንግድ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ አሳድሮ እንደነበር ጠቅሰዋል :: በኢትዮጵያ በኢነርጅ /ሃይል / እና ትራንስፖርት፣ መሰረተ ልማት በተለይም የአገር ውስጥ አየር ማረፊያዎችን የአገር ውስጥ አየር ማረፊያዎችን መገንባት ላይ እደሎች እንዳሉ አይተናል ብለዋል ::

በፎረሙ ላይ በምህንድስና ፣ በመከላከያ ፣ ግብርና ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሎጆስቲክስ ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ አስራ አራት የቼክ ሪፐብሊክ ኩባንያዎች ተገኝተው ከኢትዮጵያዊያን ነጋዴዎች ጋር በጋራ መስራት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ መክረዋል::

የኢትዮ - ቼክ የዲፕሎማሲ ግንኙነት የጀመሩት የቼክስሎቫክ (የዛሬዋ ቼክ ሪፐብሊክ) ኢምባሲ በአውሮፓዊያኑ 1955 መከፍቱን ተክትሎ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ ::

# አዲስ ቻምበርና የፓኪስታን ኤምባሲ...

ከ ገጽ 1 የዞረ

የዚህ አንዱ ማሳያ የሆነው እንቅስቃሴ በአ.አ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና አዲስ አበባ በሚገኘው የፓኪስታን ኤምባሲ መካከል የተጀመረው ተቀራርቦ የመስራት ፍላጎት አንዱ ነው:: በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የኢኮኖሚ ግንኙነት ወደ ተጨባጭ እንቅስቃሴ ለመቀየር የሚያስችል የውይይት መድረክ ተካሂዷል:: ውይይቱ የተካሄደው በአዲስ ቻምበር ዋና ጸሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም እና በኢትዮጵያ የፓኪስታን አምባሳደር አቲፍ ሸሪፍ መካከል ነው:: በውይይታቸው ወቅት የምክር ቤቱ ዋና ጸሀፊ አቶ ሺበሺ ምክር ቤታቸው በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር ይበልጥ ለማጠናከር በሀገራቱ የሚገኙ የኢንቨስትመንትና የንግድ እድሎችና እምቅ ሀብቶች በአግባቡ ሊተዋወቁ እንደሚገባ ጠቁመዋል::

ከዚህም በተጨማሪ ንግድና ኢንቨስትመንትን ሊያስፋፉ የሚችል የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ማሻሻል ላይ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል ብለዋል:: በሁሉቱ ሀገራት መካከል የጋራ የውይይት መድረክ በማመቻቸት የገበያ ትስስር የሚጠናከርበትን እድል መፍጠር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል::
በኢትዮጵያ የፓኪስታን አምባሳደር አቲፍ ሸሪፍ በበኩላቸው በሁለቱ ሀገራት መካከል ሰፊ የቢዝነስና የኢንቨስትመንት እድሎች እንዳሉ የተናገሩ ሲሆን ይህን እድል ወደ ተጨባጭ ተግባር ለመቀየር መሰራት አለበት ብለዋል::

ኢትዮጵያን ምቹ የኢንቨስትመንት አማራጭ ለማድረግ የሰራተኞችን የሙያ ክህሎት ማሻሻል እንዲሁም የውጭ ሀገር ኢንቨስትመንት ትርፍ አመቺ በሆነ መልኩ ለባለሀብቶች የሚዳረስበት መንገድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ያሉት ደግሞ በኢትዮጵያ የፓኪስታን ኤምባሲ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር ሚኒስትር ሙኒር ሳዲቅ ናቸው::

በሁለቱ ተቋማት መካከል የተደረገው የውይይት መድረክ አዲስ ቻምበር የፓኪስታን ባለ ሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ እያደረገ ያለውን ጥረት ኤምባሲው አድንቋል:: እ.አ.አ በመጋቢት 2023 የፓኪስታን የንግድ ልኡክ አዲስ አበባ በመምጣት ከኢትዮጵያውያን አቻቸው ጋር የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር እንዲፈጠር የአዲስ ቻምበር ሚና ጉልህ መሆኑ ተነስቷል::

# የብረታብረት ኢንዱስትሪው ሰሞነኛ ፈተና



ሰሞኑን ከብረት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ የብዙ መገናኛ ትኩረትን የሳበ እና ሰሞነኛ መነጋገሪያ ጉዳይ ሆኖ ሰንብቷል:: በተለይ የኢትዮጵያ መሠረታዊ የብረታብረት እና ኢንጂነሪን ማሕበር ሰሞኑን በሕገወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ ገብቷል ስለተባለው ብረት ጉዳይ ለመነጋገር አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ጠርቶ በጉዳይ ላይ ተነጋግረውበታል:: የማሕበሩ መሪዎች የብረታብረት ኢንዱስትሪውን አስመልክተው ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል:: የጋዜጣው መግለጫ ገዢ ሃሳብ በቅርቡ በሕገውጥ መንገድ ገብቶ በአገር ውስጥ ገበያ ተሰራጭቶ እየተቸበቸበ ነው ስለተባለው ብረት ጉዳይ ነው:: የማሕበሩ መሪዎች እንደሚሉት የአገራችን ኢንዱስትሪዎች ትልቁ እና ዋነኛው አንቀሳቃሽ ሞተር ብረት በሕገወጦች የሕልውና አደጋ ተጋርጦበታል ስለዚህ ጉዳዩን መነግሥት ተከታትሎ ፤ እርምጃ እንዲወስድ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ይፋ አድርገዋል::

በኮንትሮባንድ እና በሎሎች ህገወጥ መንገድ የብረታብረት ምርቶች ወደ አገር ቤት ገብተው እንደሚሸጡ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎች በሰጡት መግለጫ ላይ በስፋት ገልጸዋል:: በተለይ ከቀረጥ ነጻ ፈቃድ ሰበብ አስፈላጊ ከሆነው መጠን በላይ ጨምረው በማስገባት ገሚሱን ከተፈቀደለት ተግባር ውጪ በማዋል ህጋዊ እና ግብር ከፋይ የሆነውን ብረት ነጋዴ ከስራ ውጭ እያደረጉት እንደሆነ ተገልጿል::

የመሠረታዊ ብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ማሕበር አባላት በተለይ ለከንስትራክሽን የሚውለው የብረት ውጤቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በመፍጠር እንደ ግንባታ ኢንዱስትሪ የመሳሰሉ ዘርፎችን ይበለጥ እንዳይጎዳ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ጥሪያቸውን አቅርበዋል::

በመሆኑም እንደ ጉምሩክ አይነት የሚመለከተው የመንግስት አካል በብረት ግብይት ላይ የታየውን ክፍተትና አደጋ ከወዲሁ የቁጥጥር እርምጃ ይወስድ ዘንድ ምክረ ሀሳብ ቀርባል::

## አዲስ ቻምበር ከሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ጋር የጋራ ስምምነት ሰነድ ተፈራረመ

**በሰናይት እሸቱ**

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸሃፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም በስነስርአቱ ላይ ሳፋሪኮም ከምክር ቤቱ ጋር የቴክኖሎጂ ብቻ ሳይሆን የእውቀት አጋር በመሆን አብረው ለመስራት ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸዋል:: በዚህም መነሻነት፡ ከወራት በፊት የተጀመረውን የአጋርነት ውይይት ወደተግባር መለወጥ የሚያስችል ስምምነት መሆኑን ጠቁመዋል::

ለስምምነቱ ትግበራም በሁለቱም በኩል ክትትል እንደሚደረግ ጠቁመዋል:: የሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ሃላፊ ክሪስ ላዛሪየስ እንዳሉት ሳፋሪኮም በከተማዋ ውስጥም ሆነ ወጣ ብሎ ስራዎችን ለመስራት ንግድ ምክር ቤቱ የነጋዴዎች ወኪል ከመሆኑ አንጻር ስትራቴጂካዊ አጋር መሆኑን አንስተው የቴሌኮም አገልግሎት የኢኮኖሚ መሻሻልን በፍጥነት ለማምጣት ወሳኝ ነው ብለዋል:: አክለውም በኢትዮጵያ ብዙ መስራት የሚችሉ ወጣቶች እንደመኖራቸው ሳፋሪኮም የቴሌኮም ግንኙነትን በማሳደግ ለብዙዎች የስራ እድል መፍጠር እንዲቻል እንደሚሰራ ገልፀዋል::

በመጨረሻም ሳፋሪኮም ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት መንገድ የባንክ እንዲሁም የቴሌኮም ዘርፍ ለውጭ ገበያ ክፍት እንዲሆን ምክር ቤቱ ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ ላበረከተው አስተዋጽኦ በድርጅታቸው ስም አመስግነዋል::

## "ምቹ የሆኑ አዋጆችን በማውጣትና በመተግበር የአምራች ኢንዱስትሪው ያሉበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መፍታት የግድ ይላል" አቶ ፋሲካው ሲሳይ የአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕረዚደንት



**በስታፍ ሪፖርተር**

የአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በቦርድ የተዋቀረና በ13 የተለያዩ እና የተመረጡ ዘርፎች ላይ ትኩረቱን በማድረግ የተለያዩ ተሞክሮዎችን ፣ልምዶችን ፣ስልጠናዎችን እንዲያደርጉ በማድረግ አምራች ዘርፉ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማድረግ የተቋቋመ ምክር ቤት ነው:: ይህ ተቋም በማክሮና በማይክሮ ደረጃ ትልቅ አስተዋጾ ያለው ሲሆን መንግስት ይህን ተቋም በአዋጅ እንዲቋቋም ሲያደርግ ልዩ ድጋፍ እንደሚስፈልገው ታሳቢ በማድረግ ነው:: የአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት 20ኛ አመት የምስረታ በአልን አስመልክቶ የእንካን አደረሳችሁ መልእክታቸውን ያስተላለፉት የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕረዚደንት አቶ ፋሲካው ሲሳይ ናቸው::

የአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የ20 አመታት ጉዞ በስኬትና በተግዳሮት የተሞላ ነው ያሉት ፕረዚደንቱ ምንም እንኳን ጠንካራ የአምራች ዘርፍ እንዲፈጠር ጥረቶች ቢደረጉም የተፈለገው ውጤት ተመዝግቧል ለማለት ያስቸግራል ብለዋል:: በነዚህ 20 አመታት ፣የማምረቻ ቦታ እጥረት ፣የገበያ ችግር ፣የግብአት አቅርቦት ችግር፣የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንደ ዋና ዋና ችግሮች ሆነው ቀጥለዋል ያሉ ሲሆን ሆኖም ግን ምክር ቤቱ ከመንግስት ጋር ቁጭ ብሎ በመወያየት ለመንግስት ግብአት በመስጠት ከፍተኛ ጥረት መደረጉን፣ አምራቾች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተሞክሮ እንዲያገኙ በማድረግ ስራ መሰራቱን ጠቅሰዋል::

ምክር ቤቱ ጠንካራና ተወዳዳሪ አምራች ኢንዱስትሪ በሀገሪቱ እውን እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል::

**ወደ ገጽ 5 የዞረ**

# በቡና ዘርፍ ያሉ ሴቶች ምን ይላሉ ?



**በይድነቃቸው አለማየሁ**

ቡና ከኢትዮጵያውያን ጋር ስላለው ቁርኝት ፣የታሪክ ድርሳናት፣ የቀደሙት አባቶች ፣እንዲሁም ባዕዳን እና አገር በቀል ተመራማሪዎችን ጨምሮ ብዙ ብዙ ተብሎለታል፣ ብዙ ተጽፎለታል ። ብዙዎች ስለ ቡና ሲነሳ ፣ ቡና ለእኛ ምናችሁ ነው? ተብለን ከምንጠየቅ ይልቅ ምናችሁ አይደለም? የሚለውን ጥያቂ መመለስ ይቀለናል ይላሉ ።

በአጠቃላይ ቡና ማለት የኢኮኖሚያችን የጀርባ አጥንት መሆኑና የእድገታችን ሞተር መሆኑ ይታወቃል:: ይሄ ሁሉ ቴክኖሎጂ፣ዘመናዊ ማሽነሪዎች እና መኪኖች፣ኢንዱስትሪዎች ብቻ ብዙ ፣ብዙ የምናያቸው የባሕር ማዶ ነገሮች በአብዛኛው ወደ አገር የገቡት ይኸው ቡናችን በውጭ አገር ሂዶ ተሸጦ ባገኘነው ዶላር ነው:: ለመሆኑ በቡና ቢዝነስ ሰንሰለት ውስጥ ገበሬዎችን ጨምሮ የሴቶች ድርሻ ከ70 በመቶ በላይ መሆኑን ምን ስንቶቻችን እናውቅ ይሆን?::

ሰሞኑን በአዲስ አበባ በቡና ዘርፍ ላይ ስለተሰማሩ ሴቶች አጠቃላይ ጉዳዮች የሚያጠነጥን አንድ ዓማቀፍ ሁነት ተከናውኖ ነበር:: ኢንተርናሽናል ውሜን ኢን ኮፊ ኮንቬንሽን ወይም በምዕጻሩ IWCA ዓለማቀፍ ጉባዔ ከ32 አገራት የመጡ ሴት ቡና አምራቾች፣አቀናባሪዎች ፣ላኪዎች፣ ተመራማሪዎች በአጠቃላይ በጾታቸው ሴት ሆነው የቡና ባለድርሻዎች ሁሉ በጉባዔው ታድመዋል:: ከጉባዔው አንዱ በሆነው ሴቶች ቡናቸውን የሚያስተዋውቁበት መርሃ ግብር ላይ የተሳተፉ ሴቶች የግል እና የአገራቸውን የፖሊሲ ልምዶችን አካፍለውናል:: ከአገራችን የተገኙት ጥቂቶች ብቻ ቢሆኑም ጉባዔው መነቃቃት እና የገበያ ዕድል ለማግኘት መቻላቸውን ነገረውናል::

ሮዝ ራማሉሰ ከፓፕዋ ኒው ጊኒ የመጣች በቡና ዘርፍ የተሰማራች ናት:: ከአዲስ ቻምበር ጋር በነበራት ቆይታ እንደገለጸችው "እኛ ለዓለም ገበያ የምቀርበው ቡና በሚገባ የታጠበ የቡና ፍሬ ነው:: በአገራችን ፓፕዋ ኒው ጊኒ በብዛት የሚበቅለው ዝርያ እንደናንተ አገር አራቢካ የተባለው ነው:: በገራችን ቡና ሰንሰለት ላይ ትልቁን ቁጥር የምንይዘው እኛ ሴቶች ነን ። 99 በመቶ ማለት ይቻላላል እኛ የምንልከው እንዳለ ጥሬውን ነው::

እሴት ጭምረን ብንልክ እንፈልጋለን:: በዚህ ትርዒት ላይ ብዙ ቁምነገር አግኝተናልክ፣ ቡና ዕሴት መጨረመር ቴክኖሎጂዎችንም ተመልክተናል:: ከ60 በላይ የሚሆነው ምርታችንን የምናቀርበው ለአውሮጳ ገበያ ነው:: ለሴት ቡናላኪዎች መንግሥታችን የሚያደርግልን እገዛዎች አሉ:: አንዱ ወደ አየር በአየር እና በባሕር በማጓጓዝ ይረዳናል:: በፓፕዋ ኒው ጊኒ በቡና ዘርፍ ያሉ ሴቶች ማሕበር አለን:: መሕበሩ እርጥና ደረቅ የቡና አመራረት፣እንክብካቤ፣አያያዝ እና ለውጪ ገበያ አዘገጃጀት ላይ ስልጠና እንሰጣለን:: መንግሰት እና የቡና አስተረዳደር ቦርድ አለን:: ሁለቱም አካላት በከፍተኛ ጥራት እንዳቀርብ እና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ አንድንሆን የቆጣራል ያግዘንማል" በማለት ተናግራለች::

ሌላኛዋ የውሜን ኢን ኮፊ ተሳታፊ የሆነችው ደግሞ ከአፈሪካ ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፓብሊክ የመጣች ሲሆን እንዲህ ብላለች:: ቡና በአገሬ ኮንጎ ደሞክራቲክ ሪፐበሊክ እንደ ትንሣዔ የሚታይ ነው:: ኮንጎ ወደ ቡና አምርታ ወደ ዓለም ገበያ መላክ የጀመረችው በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላ ነው:: የኛ ቡና በቅርብ አመታት ተጀምሮ በዓለም ትልቅ አውቅና አግኝቷል:: በአገራችን አንደምታውቁት ግጭቶች ይከሰታሉ:: ይህሄ ታዲያ የቡና ዘርፉን ክፉኛ እየተፈታተነው ነው:: ብዙ ቡና አምራጮች እርሻዎቻቸውን እየተው ነው:: ሴቶች የቡና ገበሬዎችም እንደዚሁ:: ሴት ቡና ላኪዎች ደግሞ ሰላማዊ ወደ ሆነውወደ ምሥራቁ የአገራችን ክፍል እየሄዱ ነው:: ይሄ ትልቁ ችግራችን ነው:: በዚህ ጉባዔ ላይ ችግራችንን አንስተናል መንግሥታችንም ችግራችንን ተመልክቶ መፍትሔ እንደሰጠን እጠየቅን ነው:: በነገራችን ላይ ኮንጎ በምዕራቡ ክፍል ሮቡስታ በምሥራቁ ደግሞ በአረቢካ የተባሉትን ሁለቱንም ዝርያዎችን ታገኝበታለህ:: የአገሬ ቡና ላኪዎች እና አቀናባሪዎች ሌላው ችግር በቂ የገበያ መረጃ አናገኝም፣ አንዱም እዚህ የተገኘነው ገበያ አላማፈላለግ ነው:: በቆይታችን ከኢትዮጵያውያን ጋር ጥሩ ቢዝነስ ግንኙነት አድርገናል:: ጉባዔውም ምርታችንን የቡና ትውልድ ሀገር በሆነችው ኢትዮጵያ ላይ ተገኝተን በአካል እንድናስተዋውቅ ረድቶናል" በማለት ተናግራለች::

ማርብሊ ቫለንታይን ጀማይካን በመወከል በሀገሯ የሚገኙ ቡና አምራቾችን በተለያዩ የአቅም ግንባታ ስራዎች በመደገፍ በቡና ንግድ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እየሰራች እንደሆነ ለአዲስ ቻምበር ሚዲያ እንዲህ በማለት ገልጻለች "በጀማይካ የምንገኘው ቻፕተር ትቁ ስራችን በሴት የቡና ገበሬዎች ላይ ለውጥ ማምጣት ነው:: እኛ ስልጠናዎችን፣ማበጠሪያዎችን ምርጥ ዘሮችን እንዲሁም ከማሳ ጀምሮ ባሉት እሴቶች የምርት አሰባሰብ እና ማከማቸት ላይ ተከታታይ ስጠናዎች አናደርግላቸዋለን:: ወደ 4 ሺሕ ለሚጠጉ ሴት ገበሬቹ በሚመች መልክ የአሰራር ማንዋል አዘጋጅተንላቸዋል:: እያንዳንዷ ሴት ቡና አምራች በቀላሉ በማንዋሉ መሰረት እየተመራች ሥልጠናዎቸን ወደ ተግባር መቀየር ያስችላታል:: ይህ ማለት የአገራችን ቡና በጥራት ተወዳዳሪ እንዲሆን ረድቶናል:: በነገራችን ላይ የኛን ቡና ጃፓኖች ይወዱታል:: 80 በመቶ የሚሆን ቡናችን የምትገዛን አገር ጃፓን ናት" ።

በቡና መገኛ በሆነው አገር ኢትዮጵያ ጉባዔው መካሄዱ መንግሥት ቡና አምራችና ነጋዴ ሴቶችን ትኩረት የበለጠ የፖሊሲ ድጋፍ እንዲያደርግ የውሜን ኢን ኮፊ ኢትዮጵያ ቻፕተር አስተያየታቸውን አካፍለዋል:: ሌላው በዘርፉ ያሉ ሴቶች እርስ በርሳቸው የሚረዳዱበትን መድረክ እንዲያገኙ፣ በተለይ በአገራችን ሁኔታ በወንዶች ጫና ውስጥ በሚገኘው የቡና የምርት ሰንሰለት ውስጥ ሴቶች እንዴት ተጠቃሚ ይሁኑ በሚለው እና ሌሎች ተግዳሮቶችን እያነሱ የሃገራትን ተሞክሮዎች ቀምረው የመፍትሔ ሃሳቦችን እንዲያመነጩ እድል ያገኛሉ:: ሌሎች ተሳታፊዎች በበኩላቸው ቡናችንን እሴት ጨምረን የዓለም ገበያ በሚፈልገው መልከ ብዙ የሆኑ የቡና ተዋጾዎች አቅርብን ፣ የዓለምን የደረጃ እና የጥራት መሥፈርት አልፈን ጠንካራ ተወዳዳሪዎች እንድንሆን በተለይ የብድር እና የመሥሪያ ቦታዎች እንድናገኝ መንገዱን ይጥረግልን ይላሉ::

በዝግጅቱ በአብዛኛው ከቡና መካከለኛ እና መጨረሻ የእሴት ሰንሰለቶች የሚገኙ ሴቶች የተገኙ ሲሆን በማሳ ላይ የሚገኙት ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑት የአገራችን ሴቶች የሚሉትን ማካተት አልቻልንም:: በሚቀጥለው ጉባዔ እንደሚሳተፉ ተስፋ እናደርጋለን:: ይሁን እንጂ ተጠቃሚነቱ ላይ እነዚህ ሴቶች ብዙም የሉበትም:: ሴቶች የአምራችነት ድርሻቸውን ያህል ተቃሚነታቸውም ማለፊያ እንዲሆን መንግሥት ከማሕበራቸው ጋር ተቀራርቦ በመካከር፣ እንዲሁም የሌሎች አገራትን የፖሊሲ ድጋፎች እና አሰራሮችን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ በቡና ዘርፍ ላይ ላሉ ሴቶች ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት ይገባል እያልን ይህን ጽሁፍ እናበቃለን::

# "የአምራች ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው" አቶ ጫኔ ቢተው የአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ጸሀፊ



**በስታፍ ሪፖርተር**

የአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የ20ኛ አመት ክብረ በአል በመጪው ህዳር 8 2016 አ.ም እንደሚያከብር የምክር ቤቱ ዋና ጸሀፊ አቶ ጫኔ ቢተው ለአዲስ ቻምበር ሚዲያ ተናግረዋል:: የ20ኛ አመት ክብረ በአል ስኬቶችን ፤ተግዳሮቶችንና ድክመቶችን የምንገመግምበት እና ስኬቶችን ይበልጥ ለማጠናከር ፤ድክመቶችን ደግሞ ለማረምና አምራች የሆኑ አባላቶቻችንን በተሻለ ሁኔታ ለማገልግል ቃል የምንገባበት እለት ይሆናል ብለዋል::

እንደሚታወቀው ሰባ በመቶ የሚሆነው የሀገራችን ህዝብ ወጣት ነው ያሉት አቶ ጫኔ ይህን ሀብት ከተፈጥሮ ሀብት ጋር በማቀናጀት ሀገራዊ እድገት ማምጣት ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም ያሉ ሲሆን ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የዜጎች የስራ ባህል መሻሻል አለበት ብለዋል::

የባለፉት ሀያ አመታት የተቋማችን ጉዞ ከሞላ ጎደል ውጤታማ ነበር ማለት ይቻላል ያሉት አቶ ጫኔ በነዚህ በተጠቀሱት በርካታ አመታት የአምራች ዘርፉን ለመደገፍ አያሌ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያክል የአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታቸውን እንዲያሳድጉ ከልማት ባንክ ጋር በመነጋገር የማምረቻ ማሽኖችን (የሊዝ ማሽን) እንዲያገኙ ማድረግ፤ መንግስት በተወሰኑ መልኩ ለአምራቾች የማምረቻ ቦታ እንዲሰጣቸው ማድረግ ከዚህም ባለፈ የታክስ ጉዳዮችን ከመንግስት ጋር በመነጋገር ችግሮች እንዲፈቱ እገዛ ማድረግ፤ የአምራች ኢንዱስትሪውን አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች መስጠት፤የአምራች ኢንዱስትሪውን ገበያ ለማስፋት የሚያስችሉ ኢግዚቢሽንና ባዛሮችን የማዘጋጀትና አምራቾች የውጭ ሀገር ልምዶችን እንዲቀስሙ የሚሉት ይገኙበታል ብለዋል::

ምንም እንኳን በባለፉት አመታት የአምራች ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በርካታ ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም የታቀዱ ግቦችን ከማሳካት ረገድ አሁንም ክፍተቶች እንዳሉ ተቋማችን በጽኑ ያምናል ብለዋል:: ለአብነትም ያክል የአምራች ኢንዱስትሪው የማደግ አቅም ያለው ቢሆንም የፋይናንስ ችግር፤ የማምረቻ ቦታ እጥረት የመሳሰሉት አሁንም ሙሉ በሙሉ ያልተፈቱ ችግሮች እንደሆኑ ተናግረዋል::

እነዚህ ችግርች ስልታዊ በሆነ መልኩ ለመመለስ የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን በተለይም ተቋማችን የአምስት አመት የስትራቴጂክ እቅድ በመንደፍ እና ተግባራዊ በማድረግ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል::

የአምስት አመቱ የስትራቴጂክ እቅድ አለምአቀፍ ተሞክሮዎችን በማምጣት ለሀገር ውስጥ አምራቾች ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማድረግ ተሰሚነት ያለው የአምራች ዘርፍ እንዲፈጠር አላማ ያለው ነው:: በሁለተኛ ደረጃ በተቀመጠው የስትራቴጂክ እቅድ አማካኝነት የአምራች ኢንዱስትሪው አመቺ የሆነ ፖሊሲ እንዲወጣ ተጽእኖ መፍጠር ፤አለምአቀፍ የትብብር መንገዶች እንዲጠነከሩ በመስራት ላይ እንገኛለን ብለዋል አቶ ጫኔ::

ከዚህም ባለፈ በቀጣይ አመታት የአምራች ኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የምርት ጥራት ላይ መስራት የተቋማችን አንዱ እቅድ ነው:: በሚቀጥሉት አመታት የአምራች ዘርፉ የኩባንያ ማህበራዊ ሀላፊነትን የሚወጣ የሰራተኞችን መብት የሚጠብቅ እና ለአከባቢ ጥበቃ የሚቆረቆር እንዲሆን የሚያስችል ስራዎች ተቋማችን ለመስራት እቅዶችን ይዟል በማለት ተናግረዋል::

የአዲስ አበባ ዘርፍ ምክር ቤት በሚቀጥሉት የእቅድ አመታት በግሉ ዘርፍና በመንግስት መካከል እንደ አገናኝ ድልድይ ሆኖ ማገልገሉን እንዲቀጥልና በትምህርት ተቋማትና በኢንዱስትሪዎች መካከል ያለው ትብብር እንዲጎለብት ይሰራል ያሉ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ተቋማችን ፍትሀዊና ተደራሽነት ያለው የታክስ አስተዳደር እንዲኖር ፤ በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል ያለው ትብብር እንዲጠናከር በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል ብለዋል::

ከዚህም ባለፈ ተቋማችን የአምራች ኢንዱስትሪው ያሉበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በውይይት እንዲፈቱ የሚያስችል የጋራ መድረኮች እንዲመቻቹ የሚያስችል የምክክር መድረኮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፤ መንግስት ለአምራቹ ህብረተሰብ ምቹ የሆነ እና ለዘላቂ እድገት አስተዋጾ ሊያደርጉ የሚችሉ የህግ ማእቀፍ ፤ህጎችና አዋጆች እንዲወጡና ተግባራዊ እንዲደረጉ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል::

በአጠቃላይ የአምራች ዘርፉ ተወዳዳሪና ለሀገር ምጣኔ ሀብታዊ እድገት የሚያበረክተው አስተዋጾ ከፍ እንዲል ከተፈለገ መንግስት የአምራች ኢንዱስትሪዎችን በደንብ በመደገፍ እና ያሉባቸውን አስተዳደራዊ ጫናዎችንና ቢሮክራሲዎችን መቀነስ ለነገ የሚተው አይደለም በማለት መልክታቸውን አስተላልፈዋል::

## "ምቹ የሆኑ አዋጆችን በማውጣትና በመተግበር የአምራች ኢንዱስትሪው ያሉበትን ...

**ከ ገጽ 4 የዞረ**

በተለይም አድቮኬሲን እንደ አንድ ቁልፍ መሳሪያ በመጠቀም አመቺ የሆኑ ህጎችና ደንቦች እንዲቀረጹና ተግባራዊ እንዲደረጉ ጥረት ተደርጓል:: እነዚህ የአድቮኬሲ ስራዎች አምራች ኢንዱስትሪውን በግብር ጉዳይና፤በንግድ ፍቃድ እድሳት ፤ትልቅ ስራዎች ተሰርተዋል በማለት ተናግረዋል::

በኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ የንግድ አዋጅ የተሻሻለበት የእድሜ ዘመን ረዘም ያለ ነው ያሉት አቶ ፋሲካው ከብቃትና ከሰርተፊኬት ጋር ተያይዞ አምራቹ እንዳይሰራ የተደረገበት ሁኔታ እንደነበር አስታውሰዋል:: በሆቴል ዘርፍ ፤በጋራዥ ዘርፍ የወጡ መስፈርቶች ከዚህ ቀደም የነበሩ አምራቾችን ከጨዋታ ውጪ የሚያደርግ ነበር:: አምራች ዘርፉ ሊሰራ የማይችልበት ሁኔታ ውስጥ እንደነበር ያስታወሱት ፕረዚደንቱ በወቅቱ ይህን ጉዳይ ለመንግስት በማስረዳት ሂደቱ ቀስ በቀስ እየተሻሻለ እንዲሄድ በማድረግ ትልቅ የአድቮኬሲ ስራ ተሰርቷል ብለዋል:: የአውቶ ኢንዱስትሪው በሚወጡ ህጎች ምክንያት እንዳይጎዳ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ የላይሰንሲግ ጉዳይ ትኩረት እንዲያገኝ ስራ ተሰርቷል ያሉ ሲሆን የንግድ ፍቃድ እድሳት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዲፈቱ በማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል:: በዋናነት ደግሞ የኛ ተቋም የወከለው ከታክስ ጋር ተያይዞ ቅሬታ ሰሚ ጉባኤ ላይ ከታክስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን አድቮኬት በማድረግ ችግር ያጋጠማቸው ሰዎች መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል ብለዋል አቶ ፋሲካው::

አምራች ኢንዱስትሪውን በተለያዩ ጉዳዮች ለመደገፍ የተደረገ ጥረት ቢኖርም በርካታ ስራዎች ይቀራሉ፤ ማህበራት በስራ እድል ፈጠራ ዙርያ ፤በወጪና ገቢ ንግድ ፤በአቅርቦት ፤በኢምፖርት ሰብስቲትዩሽን ዙርያ ትልቅ ድርሻ አላቸው በተለይም ደግሞ በፈጠራ ዙርያ በማለት ተናግረዋል:: ነገር ግን ይህን ጠቅለል አድርገን ስናየው ትልቅ ክፍተት አለ ያሉ ሲሆን ለእንደዚህ አይነት ተቋማት የሚሰጠው ቦታ አነስተኛ መሆኑን ተናግረዋል:: ማህበራት ከተደራጁ በኋላ ክትትል ላይደረግላቸው ይችላል:: ስለሆነም ምቹ የሆኑ አዋጆችን በማውጣትና በመተግበር የአምራች ኢንዱስትሪው ያሉበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መፍታት የግድ ይላል ብለዋል አቶ ፋሲካው::

በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል ያለውን አጋርነት በማጠናከር የአምራች ኢንዱስትሪውን መደገፍ እንዲሁም በመንግስትም ሆነ በግሉ ዘርፍ በኩል ያለውን አመለካከት መቀየር ያስፈልጋል በማለት ተናግረዋል:: ለአምራች ኢንዱትሪው ልዩ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፤ይህ ዘርፍ ሲቀየር አገር ይቀየራል፤ ከአየር ባየር ንግድ ለመውጣት አመለካከትን መቀየር ያስፈልጋል በማለት ተናግረዋል::

የአምራች ዘርፍን ዘላቂ በሆነ መልኩ ችግሩን ለመፍታት ከተፈለገ በቦታ አቅርቦት፤ቤቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ፤ በፋይናንስ እና በላይሰንሲንግና ግብር አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ እንዲሁም የአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ እነዚህን አገልግሎቶች ከመንግስት ስትራቴጂ ጋር አብሮ በማዋሃድ ዘላቂ የሆነ አምራች ኢንዱስትሪን መፍጠር ይቻላል ብለዋል አቶ ፋሲካው:: ይህ ተግባራዊ እስካልተደረገ ድረስ የሀገራችን እጣ ፈንታ በውጭ ሀገር ምርት ላይ ጥገኛ መሆን ነውና የአምራች ኢንዱስትሪው ለስራ እድል ፈጠራ የሚኖረውን ሚና በሚፈለገው መልኩ ልናሳድግ አንችልም በማለት ስጋታቸውን አካፍለዋል::

በመጨረሻም የሀያኛ አመት በአላችንን ስናከብር ውድ ጊዜያቸውን ፤ገንዘባቸውን እና እውቃቸውን ለተቋማችን ለሰጡ ዜጎች ምስጋና ለማቅረብ እንወዳለን ያሉ ሲሆን አምራች ኢንዱስትሪው ያሉበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መንግስት ጋር እንዲደረስ ያደረጉ ሁሉ ሊመሰገኑ ይገባል በማለት አክለው ተናግረዋል:: ይህ ዝግጅት እውን እንዲሆን ትብብር ላደረጉ ሁሉ ለክፍለ ከተማ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች፤ ለምክር ቤቱ ሰራተኞች፤ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፤ ለአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከፍተኛ ምስጋና ለማቅረብ እንወዳለን ብለዋል::

በአጠቃላይ የሀገራችን እጣ ፈንታ መሰረቱን ያደረገው በአነስተኛና መካከለኛ አምራቾች ላይ ነው ያሉት አቶ ፋሲካው እነዚህ ተቋማት በሀገራችን እድገት ላይ የማይተካ ሚና አላቸው ብለዋል:: የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ሀያ አመት ተጉዟል አሁንም ይቀጥላል ፤ ስለሆነም አባላት የራሳቸውን ጥቅም በማስከበር በዘርፍ ምክር ቤት ያላቸውን ሚና ከመቼውም ጊዜ በላይ በማሳደግ ድርሻቸውን እንዲወጡ አቶ ፋሲካው ጥሪያቸውን አቅርበዋል::

# የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ እድሎችና ፈተናዎች



እጹብድንቅ ስለሺ(ዶ/ር)

ቱሪዝም በዋናነት ለውጭ አገር ዜጎች አገልግሎት መሸጥ ነው:: ያገር ዉስጥ ለአገር ዉስጥ ጉብኝትም አለ:: ይህ ዘርፍ በአለም ላይ በትሪሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገቢ በያመቱ የሚያመነጭ እንቅስቃሴ ሲሆን ለትናንሽ ደሴት አገሮች እንደ ዋና የገቢ ምንጭ ነው ለማለት ይቻላል::ብዙ አገሮች በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቱሪስቶችን በማስተናገድ ከሆቴል፣ ከትራንስፖርት፣ ከመግቢያ ክፍያ እና ከሌሎች የጉዞ ጋር በተገናኘ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላሮችን ይሰበስባሉ:: የዓለም ቱሪዝም ድርጅት እንደገለጸው፣ ከባለፈው ጥር እስከ ሀምሌ ባሉት ጊዜያት የዓለም አቀፍ ቱሪዝም ከኮቪድ 19 ከነበረበት አንጻር ደረጃው ወደ 84 በመቶው በማገገም ላይ ነው:: በተጠቀሱት ወራት ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ወደ 700 ሚሊየን ሰዎች ለጉብኝት ተጉዘዋል ተብሎ ይታሰባል :: ሆኖም በ 2011 አ.ም ይህ ቁጥር ለተመሳሳይ ጊዜ 833 ሚሊዮን ነበር:: በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም እንደ የእርስ በርስ ግጭት፣ የፖለቲካ ውጥረት፣ የእርስ በርስ ጦርነት እና የድንበር አቋራጭ ግጭቶች ምክንያት ማገገሚያው በአገሮች በተመሳሳይ ፍጥነት እያደገ አይደለም:: ከህዳር 2013 ጀምሮ በኢትዮጵያ ያለውን የፖለቲካ አለመረጋጋትና ግጭት በሱዳን በሁለቱ ወታደራዊ ክፍሎች መካከል ያለው ግጭት፣ የሩስያ - የዩክሬን ጦርነት እና የጋዛና የሃማስ - የእስራኤል ጦርነትን መጥቀስ እንችላለን:: እነዚህ ሁሉ ግጭቶች በአለም የጉብኝት ዘርፉ እድገት፣ ስብጥር እና አጠቃላይ ስፋት ላይ ተጽእኖ ይኖራቸዋል ተብሎ ይጠበቃል:: ስለ ኢትዮጵያ የጉብኝት ዘርፉስ ምን እንበል?

የኢትዮጵያ የቱሪዝም አቅም አነስተኛ ጥቅም ላይ ከዋሉት ዘርፎች መካከል አንዱ ነው ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል:: ወረርሽኙ ከመከሰቱ በፊት ወደ 812 ሺህ የሚጠጉ የዉጭ አገር ጎብኝዎች ወደ ኢትዮጵያ ተጉዘዋል ተብሎ ይገመታል:: የኢትዮጵያ ከስምንተኛው አለም ጋር በዓለም ላይ ካሉት ምርጥ ታሪካዊ ስፍራዎች ተርታ የምትሰለፍ በመሆኗ እነ ላሊበላ፣ የአክሱም ሀውልቶች፣ የፋሲል ቤተ መንግስት፣ የጀጎል ግንብ፣ የጉባኤ ጉብኝት እና ሌሎችም በአስር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቱሪስቶችን ሊስብ ይችላል ብሎ መከራከር ይችላል::

ከታሪካዊ ሀብቷ በተጨማሪ የተፈጥሮ መልክዓ ምድሯ ብዙ ማራኪ እና ልዩ ልዩ የምግብ እና የባህል ክብረ በዓላት እምቅ የቱሪዝም ሀብቶች በመሆናቸው ኢኮኖሚው በአግባቡ ጥቅም ላይ ካዋላቸው በአመት በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠር ብር ለማግኘት ይረዳል:: ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተገለፀው ቱሪዝም ለፖለቲካ አለመረጋጋት በቀላሉ እጅ እና ትኩረት ከሚሰጡ የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ ነው:: በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ግጭቶች ባይኖር ኖሮ የቱሪዝም ማገገሙ ፈጣን ሊሆን ይችላል ብለን መከራከር እንችላለን:: የመንገድ ደህንነት፣ የመድረሻ አካባቢ እና የመመለሻ መስመር እርግጠኝነት፣ ትክክለኛ የአገልግሎት አቅርቦት እና እነዚህ ሁሉ ቱሪስት ቦታን ለመጎብኘት ቢወስንም ባይወስንም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው::

ቱሪዝም ደረጃውን የጠበቀ የኢኮኖሚክስ መርሆውችን (የቱሪዝም አቅርቦት እና የቱሪዝም ፍላጎት) ተጠቅመን ከተመለከትን የፖለቲካ አለመረጋጋት በሁለቱም በኩል (ፍላጎት እና አቅርቦት) በኩል ጉዳት ያደርሳል:: ሆቴሎች፣ አስጎብኚዎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች፣ ትክክለኛው የሚጎበኙ ቦታዎች ክፍት መሆን በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሱ የመሄድ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው:: የመስህብ ቦታዎች እራሳቸው ለጥፋት ሊጋለጡ ይችላሉ :: እነዚህ ሁሉ የቱሪዝም አገልግሎት አቅርቦትን ማሽቆልቆል ያስከትላሉ::በፍላጎት በኩል ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ተጓዦች አነስተኛ ወጭ ወዳለበት እና ጸጥታዉ የተረጋጋ ሀገር ጉብኝት ሊያቅዱና ሊያስቡ ይችላሉ:: ይህ ሊሆን የሚችለው፣ በቀዉስ ዉስጥ ባሉ አገራት ለመጎብኘት ክፍት የሚሆኑት ውስን ቦታዎች ናቸው፣ በዚህም የተነሳ ረጅም አማራጭ መንገዶች ወደ መዳረሻ ለመጠቀም ሲገደድ፣ ለበዙ እንግልትና ወጪ ይጋለጣሉ:: ይህም ከፍተኛ የገንዘብ እና የጊዜ ወጪን እና በይበልጥ ደግሞ አለመረጋጋት እና ግጭቶች ጥላ ውስጥ ሁነው በሚያደርጉት ጉብኝት ያነሰ እርካታን ያገኛሉ ብሎ ለማሰብ ይቻላል:: ከዚህም በላይ በቱሪዝም አቅርቦት ላይ ያለው መስተጓጎል በራሱ ለተጓዦች የሚጎበኙትን ቦታ ምርጫ መወሰኛ አካል ይሆናል:: የቱሪዝም አገልግሎት ፍላጎት ማሽቆልቆሉ(እዉንም ይሁን ገና ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው) አቅራቢዎችን ተስፋ ያስቀርጣል፣ ሠራተኛ እንዲቀንሱ፣ እንቅስቃሴ እንዲገድቡ እና በአጠቃላይ አገልግሎታቸውን እንዲያቀዛቅዙ ሊያደጋቸው ይችላል:: በዚህም የዘርፉ ምጣኔ ሀብት ወደ ቀዉስ ዉስጥ ይገባል ለማለት ይቻላል:: አልፎ አልፎ እንደምናነበው፣ የተለያዩ አገራት ኤምባሲዎች በተለያዩ መጠን የጉዞ ማስጠንቀቂያ ለዜጎቻቸው ሲሰጡ በቀጥታም ይሆን በተዘዋዋሪ የቱሪዝም አገልግሎትን ፍላጎት እየቀነሱ ነው:: ዋናው ሰበብ ግን ኤምባሲዎች ሳይሆኑ ፣ ይህን እርምጃ እንዲወስዱ ያስገደዳቸው መሬት ላይ ያለ የጸጥታ ሁኔታ ነው:: ስለዚህ የቱሪዝምን አቅርቦትንም ሆነ ፍላጎት ለማስተካከል የፖለቲካ፣ የጸጥታ፣ የምጣኔሀብት እና የማህበራዊ ከባቢዎች ምቹ መሆን ይኖርባቸዋል::ቱሪዝም ለብቻዉ ተነጥሎ የሚያብብ የምጣኔሀብት ዘፍር ሳይሆን ከሌሎች አገራዊ እድገቶች ጋር አብሮ የሚያንሰራራ ወይም የሚያሽቆለቁል ዘርፍ ነው ለማለት ይቻላል::

የጸጥታ አለመረጋጋት በተለይ በአገር ውስጥ ቱሪዝም ላይ የሚያስከትለው ውጤት የበለጠ ጎልቶ የመታየት ዕድሉ ከፍተኛ ነው( ዜጎች ከቦታ ቦታ ለጉብኝት፣ ለመዝናናት ፣ ለሸርሸር የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ሁሉ):: ይህ የሚሆነው የጸጥታ አለመረጋጋት የዜጎች ገቢ እና የመግዛት አቅም እንዲቀንሱ ስለሚያደርግ ነው:: የቱሪዝም ፍላጎቶች ከገቢ ማደግ መዉረድ ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው:: የሰዎች የመግዛት አቅም ሲቀንስ፣የቱሪዝም አገልግሎት ፍላጎት ከገቢያቸው ማሽቆልቆል በላይ ይቀንሳል በመቶኛ ሲሰላ::

ለመሆኑ በኢትዮጵያ ለታመመው የቱሪዝም ዘርፍ ምን ምን አይነት መፍትሄዎች አሉ? የምርቶች ጥራትና ብዛት ለማንኛውም ዘርፍ ስኬት ቁልፍ ናቸው:: የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከትራንስፖርት ዘርፍ እንደ ኤርፖርት እና ከፍተኛ ጥራት ያላቸው መንገዶች፣ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ትላልቅ ጀልባዎች፣የሆቴል ኢንዱስትሪዎች ጥራት ያለው የምግብ እና መጠጥ ኢንዱስትሪዎች ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው ነው:: አስተማማኝ እና ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎት እና የመገናኛ ዘዴዎች ቱሪስቶች ጣቢያዎችን እንዲመርጡ፣ በችግር ወቅት ጥያቄ ቢኖራቸው ወይም እርዳታ ቢፈልጉ በቀላሉ ከሚመለከተዉ አካል እንዲግባቡ ለማድረግ የሚያስችሉ እንዲሁም መስተጋብር መፍጠር እና ስለጉዞ ልምዳቸው ያላቸውን አስተያየት መመዝገብ የሚያስችሉ አሠራሮች መዘርጋት አለባቸው:: በመሆኑም በኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ የሚተገበር ማንኛውም ተጨባጭ ጥረት ከላይ ከተጠቀሱት በርካታ ዘርፎች ጋር ያለውን ትስስር ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል:: ይህም የአየር ማረፊያዎችን፣ መንገዶችን፣ የሀይቅ ወደቦችን፣ የዲጂታል መግባቢያዎችን መገንባት ወይም ማሻሻል ሊያስፈልግ ይችላል:: በተጨማሪም ከፍተኛ ጥራት ያለው የሆቴል አገልግሎቶችን ማረጋገጥ ለነገ የማይባል ሥራ ነው:: ለምን ቢሉ በጉብኝቱ ዘርፍ ከሆቴሎች፣ መመገቢያ ቦታዎች እና መዝናኛ ቦታዎች ጥራት፣ ብዛት እና ምቹነት ጋር በጅጉ የተሣሰረ በመሆኑ ነው:: በዚህ ረገድ ሆቴሎችን በተለያየ ደረጃ መመደብ፣ አሰራራቸዉን እና አያያዛቸዉን በየጊዜው መፈተሽ ፣ ዘርፉ ዘመናዊ እንዲሆን እና አለም አቀፍ ደረጃዉን እንዲጠብቅ ልዩ ልዩ እገዛ ማድረግ ሁሉ ሊያካትት ይችላል:: እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ፍሬ እንዲያፈሩ አስተማማኝ ሰላም እና ሊተነበይ የሚችል ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ተፈጥሯዊ አካባቢ ያስፈልጋቸዋል::

ከዚህም በላይ ዓለም አቀፉ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ለጠንካራ ውድድር የተጋለጠ በመሆኑ በገበያው ላይ ልቆ ለመገኘት ገንዘብ መድቦ አስተዋዋቂ መርጦ የማስታወቂያ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል::ብዙ ሀገራት ታዋቂ ሰዎችን ቱሪስቶችን ለመሳብ እና ልዩ አገልግሎት እንዳላቸው ለአለም ለማሳወቅ እንደ ታሪካዊ ቦታዎች ፣ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ዝግጅቶች ፣የተፈጥሮ መልከአምድር እና ወደር የለሽ መስተንግዶ ወዘተ እያሉ ማማለያ ያቀርባሉ :: ግጭት እና ጦርነት ባለበት አገር ግን በአለም አቀፍ የዜና ማሰራጫዎች ተደጋግሞ የአገር ስም በአሉታዊ መንገድ ስለሚነሳ (ከአሉታዊ ማስታወቂያ ጋር እኩል ነው) :: ሰላም እና መረጋጋት ለቱሪዝም ዋና መለያ የንግድ ምልክት ነው ለማለት ይቻላል::

በኢትዮጵያ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው እንዲያብብ ሌላው ምክንያት የጥበብ ዕውቀትና ልምድን በመጠቀም የሰው ኃይልን በእንግዳ መስተንግዶ ዘርፍ ማሰልጠን ነው:: ያለበለዚያ ከቱሪዝም ኢንዱስትሪ የሚመነጨው ገቢ በመልካም አስተዳደር እጦት ይጠፋል:: ዘርፉ በባለሙያዎች መመራት አለበት፤ ህብረተሰቡ የቱሪዝም ገቢውን በሃገር ውስጥ ኢኮኖሚ ላይ በማዋል የዘርፉ ዋነኛ አካል መሆን አለበት:: የኢትዮጵያን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ለማሳደግ ተጨማሪ መንገድ ደማቅ የሀገር ውስጥ የቱሪዝም ባህልን ማዳበር ነው:: ይህም ዜጎች አገራቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ፣ በክልላዊ መስተጋብር እንዲሻሻሉ እና በዚህም የቱሪዝም ሴክተሩን ገቢ ያሳድጋል::

ለማጠቃለል ቱሪዝም በግሎባላይዜሽን አካባቢ የሚሰራ የዘመናዊ ኢኮኖሚ ዋና አካል ነው:: ነገር ግን አንድ ሀገር ከዚህ ዘርፍ የምትጠቀምበት ደረጃ በአብዛኛው የተመካው በፖሊሲዎች፣ በፖለቲካ ምህዳሩ እና በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ላይ ነው:: ጦርነቶች እና ግጭቶች የአንድን ሀገር ምቹ የቱሪስት መዳረሻ ገጽታ ያበላሻሉ:: ለጉብኝት ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣ የውጭ አገር ዜጎች ይቅርና የአገር ውስጥ ነዋሪዎች ወደ ሌሎች አገሮች ይሄዳሉ:: የተረጋጋ የፀጥታ አካባቢን ማረጋገጥ የቱሪዝም አቅርቦትንም ፍላጎትንም ያበረታታል::

# “አሁን ወደ አደግሁባት ወደ አፍሪቃ በመመለስ ላሳደገኝ ማሕበረሰብ ውለታ መክፈል እዳለብኝ ወስንኩ” ጁሊየስ ሙዋሌ



**በይድነቃቸው አለማየሁ**

ክቡራን አንባቢያን የዛሬው ዝግጅታችን የሚወስደን እዚሁ ጎረቤት አገር ነው። በአስተማሪነቱ እና በንግድ ዓለም ስለሚያጋጥሙን ፈተናዎች እና ዕድሎች መጠቀም ፣ብሎም ከስኬት ጫፍ ላይ መድረስን በጎረቤት ኬንያ የአንድ ብርቱ ሥራ ፈጣሪ ተሞክሮን አሳጥረን ልናቀርብላችሁ ወደድን።

ጁሊየስ ሙዋሌ እ.ኤ.አ በ1976 በምእራብ ኬንያ ሉንዛ በምትባል ቀበሌ ተወለደ። የመጀመሪያ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በቴሌኮሚዩኒኬሽን ምሕንድስኛ ከኮሌጅ ተመርቋል። ከዚያም የኬንያ አየር ኃይል ባልደረባም ነበር።፡ ጁሊየስ ሙዋሌ የተሻለ ሕይወት ፍለጋ ወደ አሜሪካ ያቀናል። ሕይወት በአሜሪካ ፈቷን አዙራ ጠበቀችው። በሥደት እግሩ የረገጣት ኒውዮርክ ከተማም እንደዚሁ። በኒውዮርክ ከተማ ሁሉም አልሆን ሲለው በጎዳና ተዳዳሪነት ሕይወቱን መግፋት ጀመረ። ታዲያ የዛሬውን ከበርቴ ከጎዳና ተዳዳሪነት ወደ ስመጥር ከበርቴነት የቀየረውን ሰበብ የዓለማችን ሀብታሞች ላይ ከሚያተኩረው የፎርብስ መጽሄት ባዘጋጀው ፎረም ላይ እንዲህ ብሎ ነበር “እደምታውቁት ዕድገቴ በአፍሪቃ ማለትም በኬንያ ነው። አሁን ወደ አደግሁባት፣ወደ አፍሪቃ በመመለስ ላሳደገኝ ማሕበረሰብ ውለታ መክፈል እዳለብኝ ወስንኩ” በማለት ይናገራል።

“በመጀመሪያ በተወለድኩባት መንደር አካባቢ በሰው ሀብት ላይ ኢንቨስት በማድረግ ለውጥ ማምጣት እንዳለብን ወሰንኩኝ ፣ የአዋጭነት ጥናት አጠናን ከዚያም እ.ኤ.አ በ2019 ወደ 4 ቢሊየን ዶላር አውጥተን አንድ የሕክምና እና የቴክኖሎጂ ማዕከል የሆነች ከተማ በሷት ገነባን። ይህችን ማዕከል የገነባሁት ቢያንስ አፍሪቃውያን ወደ ውጪ ሄደው መታከም የማይችሉትን እንዲሁም የሚጠብቃቸውን እጅግ ከፍተኛ የሕክምና ወጪ ለማስቀረት ነው በማለት ጁሊየስ ሙዋሌ ይናገራል።

የሙዋሌ የህክምና እና የቴክኖሎጂ ከተማ ወደ 5 ሺህ የሚጠጉ ሠራቶች አሉ። በዚህ ኢንቨስትመንት ሳቢያ ወደ 150 ኪ/ሜትር የሚሆን የአስፋልት መንገድና ወደ 3ሺህ የሚሆኑ ሶላር መብራቶች ተክለዋል። በዚህ ሁሉ ወደ 35 ሺህ የሚጠጋው የአካባቢው ሕብረተሰብ ተጠቃሚ መሆን እንደቻለ አፈሪካዊው ስራ ፈጣሪና ባለጸጋ ይናገራል።

በአሜሪካ አንዲት ትንሽ ንግድ ለመክፈት ብዙ ውጣ ውረድ እና ትልቅ ውድድር ዳጎስ ያለ ገንዘብ ጠንካራ የቢዝነስ የግንኙነት መረብ የሚጠየቅባት አገር ናት። ታዲያ እንዴት አንድ የባዕድ አገር ሰው በቀላሉ ስኬታማ ሊሆን እንደቻለ የሚለው ሃሳብ ሲነሳ የጁሊየስ ታሪክ በሕልም ውስጥ ሕልም ማየት ያህል ይሆናል። ነገር ግን ያንን ህልም እውን ማድረግ አንደሚቻል ጁሊየስ ከብዙዎች መካከል አንዱ ማሳያ ነው።

በአንድ ወቅት በኒውዮርክ ከተማ የጎዳና ተዳዳሪ እንደነበር የሚናገረው ጁሊየስ ለኒው ዮርክ ሴናተር ለነበሩት ሒላሪ ክሊንተን ለፋይናንስ ደህንነት የሚያገለግል ቴክኖሎጂ በራሱ መፍጠር እንደቻለ ባገኘው አጋጣሚ ተናግራል።

“በይለፍ ቃል አገልግሎት ይሰጥ የነበረውን ወደ ባዮሜትሪክ ሥርዓት መቀየር አንደሚያስፈልግ ሃሳብ አቀረብኩላቸው እርሳቸውም ወደ ኮንግረስ ወስደው ምክረሃሳቤን አቀረቡት። ኮንግረሱ በሃሳቤ ተስማምቶ ይኸው እ.ኤ.አ ከ2004 ጀምሮ የባዮሜትሪክ ቴክኖሎጂ በስራ ላይ ውሎ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ከዚያም ዕውቅና መጣ ፣ሥራዬን ቀጠልኩ፡ በቃ እንዲህ ነው የተነሳሁት” በማለት ጁሊየስ የህይወትና የስራ ልምዱን ያካፍላል።

ጁሊየስ በስደት የተዋት አገሩን ውለታ መክፈል የቻለ ሥራ ፈጣሪ ነው። የእርሱ የጋለ የሥራ ፍላጎት ስሜት ከአገሩ አልፎ ወደ መላው የአፍሪቃ አገራት በማስፋት ለሚሊየኖች እንጀራ ማድረስ ነው ። ይህንንም በረዥም ዕቅዱ ማሳካት አለብኝ ብሎ እየሰራ ነው።

“የረዥም ጊዜ ዕቅዴን ንገረን ካላችሁ ቀላል ነው። አፍሪቃ ወደ ትልቅ የገበያ ቦታ እየሆነች ነው፣የአፍሪቃ ነጻ ገበያ ለእኛ መልካም አጋጣሚ ነው።አፍሪቃን ለማሳደግ አንዱ የፈጠራ መብት ጥበቃ ያስፈልገናል። ይህች ከተማ የተቀናጀ የማስተር ፕላን ውስጥ ተካትታለች። የተቀናጀ ማለቴ ወደ 2 ሚሊየን የሚሆኑ የወረዳዋ ነዋሪዎች ሕይወት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሙዋሌ ስማርት ከተማ ጋር የተሳሰረ ነው ማለቴ ነው። ይህችን ከተማ ተሞክሮ ወደ ሌሎች የአፍሪቃ አገራት ማስፋፋት እንፈልጋለን። ለምሳሌ በጋና ፣በካሜሮን ሴራሊዮን፣ዛምቢያ አሁን ደግሞ በቅርቡ በሞዛምቢክ ጀምረናል። በአጠቃላይ በአፍሪቃ በተመረጡ 12 ከተሞችን መርጠን 18 ቦታዎች ስራ አንጀምራለን። ስለዚያ በዚያው ልክ የሥራ ዕድሎችን እንፈጥራለን፣የዓለም ባንክ በ2035 የ100 ሚሊየን አፍሪቃውያንን ከድሕነት ማውጣት ለያዘው እቅድ የእኛን መሰል የተቀናጀ ኢንቨስትመንት በጣሙን አስፈላጊ ነው እላለሁ” በማለት ጁሊየስ ይናገራል።

እኛም ከዛሬው ባለታሪካችን ሥራ ፈጣሪ ቁም ነገር እንዳገኛችሁበት ተስፋ እያደረግን ለዛሬ ያልነውን በዚሁ አበቃን ሰላም!

## የሳውዲ አረቢያው ኔት ገልፍ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጅ ኩባንያ በዘርፉ ከሚሰሩ የአዲስ ቻምበር አባላት ጋር በጋራ መስራት በሚችልበት ሁኔታ ላይ መከረ

**(አዲስ ቻምበር፣ ጥቅምት 28፣2016)**

የሳውዲ አረቢያው ኔት ገልፍ የአይቲ ኩባንያ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሚሰተር አህመድ ያህያ በአዲስ ቻምበር በመገኘት በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ፣ በእውቀት ሽግግርና በትብብር መስራት እንደሚፈልጉ ገልፀዋል።

ኩባንያቸው ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ዘርፍ ከተሰማሩ የአገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር በትስስርና ትብብር ለመስራት መሆኑንም ሚስተር አህመድ ገልፀዋል። የአዲስ ቻምበር ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም በበኩላቸው ሁለቱ አገራት ያላቸው ግንኙነት ረጅም አመታትን ያስቆጠረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በንግድና ኢንቨስትመንት ለመሰማራት ትልቅ እድል እንደሚፈጥር ተናግረዋል።

የሳውዲ አረቢያው ኔትገልፍ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅና ቴሌኮም ኩባንያ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ደግሞ በንግድ ላይ ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክር መሆኑን ያላቸውን እምነት ገልፀዋል ።

የሳውዲው ኩባንያ ስራ አስፈጻሚ እንደተናገሩት ወደ ኢትዮጵያ የምንመጣው ከኢትዮጵያዊያን ኩባንያዎች ጋር ያለውን ገበያ ለመሻመት ሳይሆን ትስስር እና አጋርነት ፈጥረን በጋራ መስራት እንፈልጋለን ብለዋል።

አክለውም ያላቸውን ልምድ በቴክኖሎጅው ዘርፍ የተሰማሩ ኩባንያዎች የመደገፍና ለችግሮችም መፍትሄ የመስጠት ስራ እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል ።

በውይይቱ ላይ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ አራት አገር በቀል ኩባንያዎችም ሰለ ድርጅቶቻቸውና ዘርፉ በሀገሪቱ ስላለበት ደረጃ ለኔት ገልፍ አመራሮች ገለፃ አድርገውላቸዋል።

# አዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት

ADDIS ABABA CHAMBER OF COMMERCE AND SECTORIAL ASSOCIATIONS

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት/ አዲስ ቻምበር/ ለአባላቶቹ እና ለመላው የንግዱ ህብረተሰብ በዲጂታል የታገዘ የ2024-2025 እትም የቢዝነስ ዳይሬክተሪ/ የንግድ ማውጫ/ እነሆ እያዘጋጀ ይገኛል::

ይሄው በሞባይል እና በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መተግበሪያ ዘዴዎች የተዘጋጀው የንግድ ማውጫ ፣ ለነጋዴዎች፣ ለውጪ ባለሃብቶች፣ለስራ ፈጣሪዎች፣ለውጪ ሀገር ዲፕሎማቶችና ሚሲዮኖች ፈጣን የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል::

በየሁለት አመቱ ታትሞ በሚሰራጨው እትም ላይ የድርጅትዎን ምርትና አገልግሎት በሀገር ውስጥ እና በአለም ዙሪያ እንዲያስተዋውቁ አዲስ ቻምበር በአክብሮት ይጋብዛል::

የኩባንያዎትን የቢዝነስ መረጃ በንግድ ማውጫው ላይ በማስፈር በየትኛውም የአለም ገበያ ላይ ለሚሊዮኖች ተደራሽ ይሁኑ!!!

ይቻላል It's Possible!

ንግድ ምክር ቤት ህንፃ ሚክሲኮ አደባባይ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Chamber of Commerce Building Mexico Sq. Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ/Tel: +251 115 518055 ፋክስ/Fax: +251 115 511479
P.O.Box 2458 አዲስ አበባ፣ ኢትዩጵያ/Addis Ababa Ethiopia ኢ ሜይል/E-mail: Infor@addischamber.com



# Have you registered

**for the upcoming 14th Addis Chamber International Agriculture and Food Trade fair/ AgriFex/ 2023 at the Millenium Hall, Addis Ababa?**

REGISTER NOW

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

## 14TH ADDIS CHAMBER INTERNATIONAL AGRICULTURE & FOOD TRADE FAIR

14ተኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ የእርሻና ምግብ ንግድ ትርዒት

December 7-9, 2023 (ከሕዳር 27 እስከ 29 ቀን 2016 ዓ.ም.)

14th AGRIFEX

14TH
AGRIFEX ETHIOPIA



"Maximizing Value Additions through Agro Business"

Food processing

# Addis Ababa Chamber of commerce and Sectoral associations
# Terms of reference to conduct
# “Business Leadership Training for Business Women Leading SMEs”

**I. Background**

Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectorial Associations (AACCSA) is a voluntary Business Membership Organization (BMOs) established by the General Notice Number 90/1947 as an autonomous, non-governmental, non-political, and non-profit making organization. It was re-registered as per proclamation number 341/2003 with a mission of promoting business and investment by providing demand driven services to the best satisfaction of its members and advocating for favorable business environment.

AACCSA places a special emphasis on building business communities' capacity and providing demand-driven business training to members of the local business community in order to assist them in acquiring the knowledge and skills required for success in today's challenging business environment.In line with this AACCSA has been running a project in partnership with Danish Confederation Industries which includes an intervention program to build the capacity of member business companies in general and women lead SME businesses in particular. Small and Medium Enterprises (SMEs) plays a vital role in most economies, particularly in developing countries. They account for the majority of businesses worldwide and are important contributors to job creation and global economic development. In Ethiopia the development of small and medium enterprises play a key role in Ethiopia's drive to reach middle-income country status. SMEs not only serve as important to creating job opportunities, but they also contribute to the country's economic growth, particularly as a catalyst for the shift to an industrialized society. However, there are barriers confronting the success of SMEs. While some of the constraints to SMEs growth relate to external factors over which the enterprise has less control, others relate to the leadership capacity and knowledge of SME leaders. Therefore, to address the latter constraints, working on their leadership skills development through capacity building and training is vital. Considering this, AACCSA in collaboration with Danish Confederation Industries (DI-SPAII project) plans to organize the training for its members drawn from Women Led SMEs.

**II. Objectives of the training**

The objective of the training is to enhance the capacities of women business leaders to transform themselves so that they can effectively realize their visions, to become more proactive in managing their careers, to examine their managerial skills in order to promote personal strengths at work, to examine their experience with other experience of women business leaders.

**III. Methodology**

The trainer will apply multiple techniques to properly deliver the required training and to achieve the objectives of the training. She/he is expected to use various types of methodologies like power point presentation, Group discussions, experience sharing, related demonstrations, etc.

**IV. Scope of the Assignment**

The training should cover;

- Leadership concepts and its various styles;
- Leadership in relation with Decision making, communication, negotiation, work-life balance, time management, and personal growth etc.
- Leadership Challenges with practical examples;
- Women business leadership challenges with practical examples;
- Barriers to development for women leadership;
- Way outs for the challenges/barriers with best practices;
- Opportunities of women business leaders; the unique value proposition of women in business leaders.
- Other issues that the trainer assumed to be pertinent to the area of the training;

**V. Deliverables**

The trainer is expected to deliver:

- Presentation at the training session which is estimated to be 8 hours/one full day/ for about 30 participants;
- Power point presentation slides and
- Training report within a week after the training.

**VI. Expected Results**

At the end of the training program, participants will be able to:

- Acquire the relevant leadership skill needed in different situations.
- Recognize relevance of leadership role in business management
- Question their past leadership experiences and explore new way of leadership styles
- Capture best practices in leadership
- Exchanged knowledge regarding the challenges and opportunities
- Learn and practice the skills necessary to succeed and reach goals in cooperation with the employees.
- Learn how best to match the leadership needs and demands of the employees in the organization in terms of relevant leadership and clear goals and decision making.
- Enable to address challenges facing women business leaders.
- Strengthen their leadership network
- Generally, the training is required to be impact full which the participants can be well-prepared to upgrade their business to the next level.

**VII. Duration and Venue**

The training shall be delivered for one full day (8 hours) in Addis Ababa at selected hotel.

**VIII. Selection Procedure**

Selection of candidates will be based on the financial and technical proposals.

Evaluation Criteria and Weight

- Financial evaluation – 20 %
- Technical evaluation –80%

**IX. Required qualification and experience**

The trainer is required to meet the following requirements:

- MSc/MA degree in Social science and other related fields; (25%)
- Minimum of five years' experience in conducting trainings in leadership; (50%) and.
- Experience in entrepreneurship or business development training (25%).

**X. Applications**

Interested applicants can collect the detailed ToR from Mexico Square, Chamber Building; Applicants can submit technical and financial proposals with a separate sealed A-4 Size Envelope to Procurement and Property Administration Department Chamber's building, 1st floor, office number 12. The proposal, to be submitted should be in English and shall include the following:

**A. Technical proposal**

- it incorporates understanding of the assignment, proposed methodology and approaches, short description of deliverables and candidate's qualification, demonstrated experience and exposure to the assignment.

**B. Financial Proposal indicating :**

- All costs to conduct this assignment (including VAT) in ETB.

**Contact address**
Membership Development and Support Department
Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Associations
**Tel:** 0115519817/ 0115514517/0115518055/226 **Email:** Membership.addischamber@gmail.com

Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Institute of Directors (IoD)-Ethiopia

Institute of Directors Ethiopia

## Invitation to participate on Training Program

Addis Chamber established a dedicated institute, Institute of Directors (IoD)-Ethiopia, which capacitates and professionalizes board and directors of both public and private sectors of the economy to ensure and sustain the country's economic development.

The following programs specifically designed to enhance and support the development of Board of Directors, Women on Leadership and Company Secretaries with the knowledge and competencies needed to understand board dynamics.

| No | Training Program | Date | Objective | Target Groups |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Company Secretary /CS/ | Nov. 23-24, 2023 | To upgrade CS's competency as per the new commercial law of Ethiopia. | Company Secretaries |
| 2 | Capital Market | Nov. 29-30, 2023 | To provide a contextual view about how the capital market will operate To give the essential skills on the capital market for successful wealth creation/maximization | Board of Directors, Senior Business Executives, Owners/Decision Makers |
| 3 | Women on Board | Dec. 12-13, 2023 | To enhance women leaders capacity by broaden/deepen knowledge of leadership, governance, and increase effectiveness of your team. | Women Board of Directors, women who have admitted to the Board of Directors and women leaders with the ambition and qualities to take step towards a boardroom position. |

**Don't miss out this incredible opportunity to invest in yourself and take your career to develop your skills and bring your vision to new heights. Start your journey towards professionalism and success today.**

**Venue: To be announced upon registration**
**To learn more and for registration:**
**+251 115 15 5221 / +251 913 842 645 / +251 911 458 459**
**email: iod.aaccsa@gmail.com.**
**Seats are limited; registration is on first come first served basis.**

**Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Associations (AACCSA)**

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER